The Royal Wolverhampton
NHS Trust

# በደም ወለድ ኢንፌክሽን ማጣሪያ - ለወጣቶች እና ለአሳዳጊዎች መረጃ

GEM ማእከል

በሁሉም የጤና አጠባበቅ ውስጥ የኢንፌክሽን መከላከል ዋና ቅድሚያ ሲሆን ሁሉም የሚጫወተው ድርሻ አለው።

- እባክዎን እጆችዎን በተደጋጋሚ ለ20 ሰከንዶች ሳሙና እና ውሃ ወይም የአልኮል ጄል በመጠቀም ያፅዱ።
- የተቅማጥ እና/ወይም ማስታወክ፣ ሳል ወይም ሌሎች የመተንፈሻ ምልክቶች፣ የሙቀት መጠን ወይም ማንኛውም የላብ ወይም የማሽተት አለመቻል ምልክቶች ካሉዎት እባክዎን ሆስፒታሉን ወይም ሌላ የእንክብካቤ መስጫ ቦታን አይጎበኙ፣ ከ111 ምክር ይጠይቁ።
- አካባቢውን በንጽህና ይጠብቁ
- ኢንፌክሽኖችን ከሆስፒታሎቻችን እና ከእንክብካቤ ቤቶቻችን ውስጥ ለማስቀረት በጋራ እንስራ።

ዛሬ ያገኙት ሐኪም የደም ምርመራ እንዲያደርጉ ይመክራል። የደም ምርመራው የሚከተሉትን ኢንፌክሽኖች ይፈልጋል- ሄፓታይተስ ቢ፣ሲ፣ ኤች አይ ቪ፣ እና ቂጥኝ። የደም ምርመራ ማድረ ወይም አለመወሰን የእርስዎ ውሳኔ እንደመሆኑ መጠን ምርመራውን ለምን እንደምንፈልግ መረ ለእርስዎ አስፈላጊ ነው።

# እነዚህ ኢንፌክሽኖች እንዴት ይዘውኝ ሊሆኑ ይችላሉ?

እነዚህ ኢንፌክሽኖች ሁሉም ከሰው ወደ ሰው ሊተላለፉ ይችላሉ። ኢንፌክሽኖች ከእናት ወደ ያልተወለደ ሕፃን ሊተላለፉ ይችላሉ። አንዳንድ ልጆች እስኪያድጉ ድረስ የማያውቋቸው ኢንፌክሽኖችን ይዘው ይወለዳሉ።

እርስዎ በበሽታው ከተያዙበት የዓለም ክፍል ስለሆኑ ዶክተርዎ በበሽታ የመጠቃት አደጋ ደርሶብዎ ይሆናል ብሎ ያስብ ይሆናል። ወደ እንግሊዝ በሚጓዙበት ጊዜ አንዳንድ ልጆች ተጎድተዋል ወይም በበሽታ በሚይዙበት ሁኔታ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ።

በመጨረሻም ፣ ይህ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ፣ ወይም በደም በኩል ሊከሰት ይችላል ፣ ለምሳ ኢንፌክሽኑ ከያዘው ሰው ጋር መርፌ ከተጋሩ ሊተላለፍቦት ይችላል።

# ኢንፌኽሽኑ ካለብኝ ማወቁ ለኔ ለምንድነው ጠቃሚ የሆነው?

ኢንፌክሽኑ ያለባቸው ብዙ ሰዎች፣ በተለይ ከኢንፌክሽኑ ጋር አብረው የተወለዱ ከሆኑ ለረጅም ብዙ እና ባለ ሙሉ ጤንነት ሆነው ይቆያሉ። ቢሆንም ግን ኢንፌክሽኑ ጉዳት እያደረሰባቸው ነ በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ኢንፌክሽን ሊይዝዎ ይችላል።

ሁሉም ኢንፌክሽኖች የሚድኑ አይደሉም፣ ቢሆንም ግን መድሃኒት በሽታው እንዳይብስ በማስቆ ሰዎች ጤናቸው የተጠበቀ እንዲሆን ያደርጋል። ያል ህክምና እና እንክብካቤ፣ እነዚህ ሁሉ ኢንፌክሽኖች ሰዎች በከባዱ እንዲታመሙ እንዲሁም እንዲሞቱ ሊያደርጉ ይችላ

የ HIV ህክምናዎችእጅግ በጣም ከመሻሻላቸው የተነሳ በዚህ ሰአት ረጅም እድሜ መኖር ይቻላል፣ HIV ያለባቸው ሴቶችም በቫይረሱ ያልተለከፉ ልጆች እንዲወል አስችለዋል።

በተጨማሪም ኢንፌክሽን እንዳለቦት ማወቅ አስፈላጊ ነው ፣ ምክንያቱም ለሌሎች ሰዎች መተላለፉን እንዴት ማቆም እንደሚችሉ መማር ይችላሉ።

## ምርመራው እንዴት ይከናወናል እና ኢንፌክሽን እንዳለብኝ ማን ያውቃል?

ብዙውን ጊዜ በክርንዎ አቅራቢያ በመርፌ በመጠቀም ደም ይወሰዳል። ይህ የሚከናወነው በፍሌቦቶሚስት (የደም ምርመራዎችን እንደ ሥራው የሚሰራ ሰው) የምርመራው ውጤት ብዙዐ ጊዜ በሶስት ሳምንታት ውስጥ ይመለሳል።

ዛሬ ያገኙት ዶክተር ያነጋግርዎታል። የደም ምርመራዎች እርስዎ ኢንፌክሽን እንደሌለቦት ካሳዩ ደብዳቤ ይላክሎታል። ያለበለዚያ ውጤቱን ለመወያየት ሌላ ቀጠሮ ይሰጥዎታል።

የደም ምርመራዎ ውጤት ለእርስዎ እና ለጠቅላላ ሐኪምዎ እና ኢንፌክሽኖችዎን ለማከም ለሚከታተሉዎት ሌሎች ዶክተሮች ይሰጣል። እርስዎ ካልፈቀዱ በስተቀር ማንም አይነገርም። እርስዎ ከሚያምኑት አዋቂ ጋር ለመወያየት ከፈለጉ ጤናዎን ለመንከባከብ ድጋፍ የሚሰጥ ሰው መኖሩ አስፈላጊ ነው።

## ከእነዚህ ኢንፌክሽኖች አንዱ በደሜ ውስጥ ቢገኝ ምን ይሆናል?

በልዩ ባለሙያ ሐኪም ይታያሉ። የሚያስፈልጎትን ህክምና በሚመለከት ያነጋግርዎታል ፣ በየጊዜው ጤናዎን እንዲመረምሩ ደግሞ ያመቻቹልዎታል።

## ስለ እያንዳንዱ ኢንፌክሽን ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እዚህ ያንብቡ:

## ሄፓታይተስ ቢ ቫይረስ ምንድነው?

ሄፓታይተስ ቢ በጉበት ላይ ጉዳት የሚያደርስ ቫይረስ ነው። ጉበቱን ሊጎዳ እና ሊያቆስለው ይችላል፣ አንዳንድ ሰዎች ላይ ደግሞ ወደ ጉበት ካንሰር ሊያመራ ይችላል።

## ሄፓታይተስ ሲ ቫይረስ ምንድነው?

ሄፓታይተስ ሲ ጉበትን ሊጎዳ የሚችል ሌላ ቫይረስ ነው። በአብዛኛዎቹ ሰዎች የጉበቱ ጉዳት ቀላል ነው ፣ ግን በአንዳንድ ሰዎች ላይ በአዋቂ ሕይወት ውስጥ ከባድ የጉበት ጉዳት ወይም ካንሰር ሊያመጣ ይችላል።

## ኤች አይ ቪ ምንድን ነው?

ኤች አይ ቪ ኢንፌክሽኖችን (በሽታ የመከላከል አቅም) የሚዋጋውን የሰውነት መከላከያ ስርዓት የሚያጠቃ ቫይረስ ነው። ይህ ሰውነቱን ጤናማ አካል ሊቋቋማቸው የሚችላቸውን ኢንፌክሽኖች ጋር መዋጋቱን ያቆማል።

## ቂጥኝ ምንድን ነው?

ቂጥኝ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም፣ እርጉዝ ባለችበት ጊዜ ኢንፌክሽኑ ከነበረባት ሴት ወደ ልጅ የሚተላለፍ የባክቴሪያ ኢንፌክሽን ነው። መጀመሪያ ላይ ቁስሎችን እና የቆዳ ሽፍታዎችን ሊያስከትል ይችላል ፣ እናም ሰዎች ህመም እንዲሰማቸው ያደርጋል። ካልታከመ ታዲያ አንጎልን ጨምሮ በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል እናም ለሞት ሊዳርግ ይችላል።

ከቂጥኝ ጋር የተወለዱ ልጆች አንጎልን ፣ አጥንቶችን እና ጥርሶችን ጨምሮ በብዙ የተለያዩ የሰውነታቸው ክፍሎች ላይ ጉዳት ሊደርስባቸው ይችላሉ።

ቂጥኝ አብዛኛውን ጊዜ በአንቲባዮክ ይታከማል።

## English

**If you need information in another way like easy read or a different language please let us know.**

**If you need an interpreter or assistance please let us know.**

## Lithuanian

**Jeigu norėtumėte, kad informacija jums būtų pateikta kitu būdu, pavyzdžiui, supaprastinta forma ar kita kalba, prašome mums apie tai pranešti.**

**Jeigu jums reikia vertėjo ar kitos pagalbos, prašome mums apie tai pranešti.**

## Polish

**Jeżeli chcieliby Państwo otrzymać te informacje w innej postaci, na przykład w wersji łatwej do czytania lub w innym języku, prosimy powiedzieć nam o tym.**

**Prosimy poinformować nas również, jeżeli potrzebowaliby Państwo usługi tłumaczenia ustnego lub innej pomocy.**

## Punjabi

**ਜੇ ਤੁਹਾਨੂੰ ਇਹ ਜਾਣਕਾਰੀ ਕਿਸੇ ਹੋਰ ਰੂਪ ਵਿਚ, ਜਿਵੇਂ ਪੜ੍ਹਨ ਵਿਚ ਆਸਾਨ ਰੂਪ ਜਾਂ ਕਿਸੇ ਦੂਜੀ ਭਾਸ਼ਾ ਵਿਚ, ਚਾਹੀਦੀ ਹੈ ਤਾਂ ਕਿਰਪਾ ਕਰਕੇ ਸਾਨੂੰ ਦੱਸੋ।**

**ਜੇ ਤੁਹਾਨੂੰ ਦੁਭਾਸ਼ੀਏ ਦੀ ਜਾਂ ਸਹਾਇਤਾ ਦੀ ਲੋੜ ਹੈ ਤਾਂ ਕਿਰਪਾ ਕਰਕੇ ਸਾਨੂੰ ਦੱਸੋ।**

## Romanian

**Dacă aveți nevoie de informații în alt format, ca de exemplu caractere ușor de citit sau altă limbă, vă rugăm să ne informați.**

**Dacă aveți nevoie de un interpret sau de asistență, vă rugăm să ne informați.**

## Traditional Chinese

如果您需要以其他方式了解信息，如易读或其他语种，请告诉我们。

如果您需要口译人员或帮助，请告诉我们。

Designed & Produced by the Department of Clinical Illustration,
New Cross Hospital, Wolverhampton, WV10 0QP Tel: 01902 695377.

Review Date 27.02.2028 Date Produced 2021 MI_8773214_02.07.25_V_2